# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር

www.eotcipc.org

## መግለጫ

### በኢየሩሳሌም ስለሚገኘው ታሪካዊ የኢትዮጵያ ገዳም

እንደሚታወቀው፤ ልዩ ስሙ፤ “ዴር ሡልጣን” በመባል የሚታወቀው፤ ኢየሩሳሌም የሚገኘው ታሪካዊው የኢትዮጵያ ገዳም ከፍ ያለ ችግር ላይ ወድቋል። የችግሩም ዋናው ምክንያት፤ “status quo” (ስቴተስ ኮ) በሚባለው የኦቶማን ቱርኮች አካባቢውን በሚገዙበት ዘመን በደነገጉት ውሳኔ መሠረት፤ በገዳሙ ላይ ምንም ዓይነት ጥገና እንዳይከናወን ተከልክሏል በማለት የእሥራኤል መንግሥት በወሰደው አቋም በጊዜ ብዛት፤ የገዳሙ ሕንጻዎች ወደ መፈራረስ አደጋ የተቃረቡ መሆኑን በመሐንዲስ በተከናወነ ምርመራ በመረጋገጡ ነው።

ለገዳሙ ጥገና የሚያስፈልገው ተግባር እንዳይከናወን ችግር ፈጥሮ የቆየው ሌላው የሚያስቆጭ ምክንያት፤ የግብጽ ኮፕቶችና መንግሥት በገዳሙ ላይ መሠረት በሌለው

የይገባኛል ባይነት ለእሥራኤል መንግሥት የሚያቀርቡት ተቃውሞ ነው።

ከላይ በተጠቀሱት አግባብነት በሌላቸው ምክንያቶች፤ የገዳሙ ሕንጻዎች ለመፍረስ በመቃረባቸው፤ በገዳሙ የሚጠቀሙት መነኮሳትና ካሕናት እንዲሁም ምእመናንና ሌሎች ጎብኚዎች አደጋ ላይ ሊወድቁ በሚያሰጋበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።

በኦቶማን ቱርኮች ዘመን በተደረገ ውሳኔ፤ ገዳሙ እንዲፈርስ ማድረግ ኢፍትሐዊ የሆነና በፍጹም ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ፤ በማሕበራችን ድረ-ገጽ በwww.eotcipc.org የሚገኘውን ለተከበሩ የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የሚላከውን አቤቱታ በመፈረም፤ ታሪካዊው የኢትዮጵያውያን ገዳም ተገቢው ጥገና ተከናውኖለት ቅርሳችን እንዲድንልን በዓለም ዙሪያ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች እንድንተባበር አደራ እንላለን።

ቸሩ የኢትዮጵያ አምላክ ይርዳን።